መስከረም 1 2001 ልዩ እትም

# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ፡የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org



## " ነፃነታችን በተጋነነ ቀረጥ አይታፈንም" ሶስት ጋዜጦች በአንድ ጊዜ ከህትመት ውጪ ሆኑ

አፋኙ እና ጨቋኙ የፕሬስ ህግ በፀደቀ ማግስት፤ በአዲስ መልክ ህትመት ከጀመሩትና በጣት ከሚቆጠሩት ጥቂት ነፃ ጋዜጦች መካከል ሶስቱ ስራቸውን አቆሙ።በአቶ በረከት ፌታውራሪነት የሚመራው የነፃ ፕሬስ አጥፊ ግብረ ሀይል፤ጋዜጦቹን ከህትመት ውጪ እንዲሆኑ ያደረጋቸው፤ ሆን ብሎ በማተሚያ ዋጋ ላይ የተጋነነ ዋጋ እንዲጨመር በማድረግ ነው።ይህ ግብረ ሀይል ፕሬሱን ለማጥፋት ከሚወስዳቸው ፖለቲካዊ እርምጃዎች አንዱ፤ገዥው ፓርቲ በሞኖፖል በያዛቸው የህዝብ መገናኛ ብዙሀኖች አማካይነት ነፃ ፕሬሶችን ማጥላላት ሲሆን ፤በታክስ በማሳበብ የህትመትን ዋጋ ማሻቀብ ደግሞ እንደ ኢኮኖሚያዊ እርምጃ ከተነደፉት የማጥፊያ ስልቶቹ አንዱና ዋነኛው መሆኑን ከማስታወቂያ ሚኒስቴር አካባቢ የደረሱን ተጨባጭ መረጃዎች ያመለክታሉ።

በተነደፉት ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች ሊጠፉ ባልቻሉት እና በይዘታቸው የገዥውን ፓርቲ አጠንክረው በሚተቹ ላይ ህጋዊ እርምጃ መውሰድ በፖሊሲ ደረጃ የተቀመጠ መሆኑን ራሳቸው አቶ መለስ በፃፉትና ባለፈው ሳምንት በድርጅታቸው ስብሰባ ላይ ለውይይት ባቀረቡት ሰነድ ላይ ሰፍሯል።እንደውም አቶ መለስ በዚህ ሰነዳቸው፦ በአሁኑ ጊዜ የግሉ ሚዲያ ለፓርቲያቸውና ለስልጣናቸው ያለውን አደጋ ሲያትቱ ፤"ከግንቦቱ ምርጫ በከፋ መልኩ እየተገለፀ ይገኛል"ማለታቸው፤ሰውየው ምን ያህል ድንጋጤ ውስጥ እንደገቡ እና እረፍት የነሷቸውን እነኚህን ጥቂት ጋዜጦች ለማጥፋት እንቅልፍ እንደማይኖራቸው የሚያመላክት ነው ብለዋል- መረጃውን ያደረሱን እና ስብሰባውን የተሳተፉ ወገኖች።

ይህንኑ ተከትሎ የብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት የንግድ መምሪያ ስራ አስኪያጅ አቶ አዳሙ ሀይሌ ሰሞኑን ለየጋዜጦቹ በፃፉት ደብዳቤ የዓለም የወረቀት ዋጋ እና ታክስ እንደጨመረ በመግለፅ፤ ከአዲሱ ዓመት መግቢያ ከመስከረም አንድ ጀምሮ የማተሚያ ዋጋ እንደሚጨመር አስታውቀዋቸዋል።ለጊዜው የጭማሪውን መጠን ለማረጋገጥ ባንችልም፤አንዳንድ ወገኖች የህትመት ጭማሪው ሀምሳ በመቶ ነው ሲሉ ፤አንዳንድ ወገኖች በእጥፍ መጨመሩን ይናገራሉ። በአማካይ የኢትዮጵያ ጋዜጦች የኢኮኖሚ አቅም ሲታይ፤ አሁን ለህትመት እየከፈሉት ባለው ከፍተኛ ዋጋ ላይ የ 5 እና 10 ፐርሰንት ጭማሬ ማድረግ በጣም ብዙ መሆኑን የሚናገሩት የዘርፉ ሙያተኞች፤ከዚያ በከፋ መልኩ በግማሽና በእጥፍ ዋጋውን መስቀል በቀጥታ " ስራችሁን አቁሙ" ብሎ እንደማዘዝ ነው ብለዋል።በዚህም ምክንያት ትናንት በይፋ ከህትመት ውጪ መሆኑን ያስታወቀውንና በጋዜጠኛ ወሰንሰገድ ገብረ ኪዳን የሚታተመውን "ሐራምቤ" ን ጨምሮ ሦስት ጋዜጦች ሥራቸውን አቁመዋል።

ሀሳብን በነፃነት ከመግለፅ ህገ መንግስታዊ መብት ጋር በቀጥታ የተያያዘው የወረቀትና የህትመት ጉዳይ፤ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን በሚከተሉ እጅግ በርካታ አገሮች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ የሚደረግለት ሲሆን፤ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አምባገነኖች በነገሱባቸው ጥቂት አገሮች ደግሞ ይህ ተፈጥሮአዊና ዜግነታዊ መብት በተደጋጋሚ በታክስና በቀረጥ ሲገሰስ መስተዋሉ እጅግ አሳዛኝ መሆኑን ይናገራሉ -የአዲስ አበባ ነዋሪዎች። ⟶

ነዋሪዎቹ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት አስተያየት፦" እየተወሰደ ያለው እርምጃ አጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ አፍኖ ለመግዛት እንደ አዲስ የተጀመረው እንቅስቃሴ አካል ነው።የተለያዩ ሀሳቦችን የሚያንሸራሽሩ ጥቂት ጋዜጦችን የተጋነነ ዋጋ በመጨመር ድራሻቸውን ለማጥፋት የተነደፈው ስልት የሚያዋጣ አይደለም።የዲሞክራሲን ጣዕም የቀመስነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከእንግዲህ ወደ ሁዋላ አንልም።እንኳዋን በታክስ፤ በግድያና በእስራት ነፃነታችን አልታፈንም፣አይታፈንምም" ብለዋል።

## አጠቃላይ እንቅስቃሴ ቆሟል የሃገሪቱ ኢንቨስትመንት ሁኔታ አሁንም የባለሃብቶችን እምነት አላገኘም

አዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ባለፈው ዓመት ፈቃድ ከወሰዱ 1 ሽህ 269 ባለሀብቶች፤ ሥራ የጀመረው አንዱ ብቻ መሆኑን ከአዲስ አበባ አስተዳድር ኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የወጣ መረጃ አመለከተ። በኩማ ሚዴቅሳ የሚመራውና የአዲስ አበባ ህዝብ ላይ ያለ ፍላጎቱ የተጫነው የሀይል አስተዳደር፤ከተማይቷን ለማሳደግና የከተማዋን ነዋሪዎች ኢኮኖሚያዊ አቅም ለማጎልበት ሁኔታዎች ስለተመቻቹ በቀጣይ ፈጣን እንቅስቃሴ እንደሚካሄድ ቃል በገባበት ዓመት፤ ከዚያው መስተዳድር የወጣው ይህ መረጃ ተቃራኒውን ማመላከቱ ለብዙዎች አስገራሚም፣ አስቂኝም ሆኗል።፣ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## የግንቦት 7 ንቅናቄ አጭር ሞገድ ሬድዮ ስርጭት ዛሬ መስከረም 1፣ 2001 ዓም ይጀመራል

ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም
ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ17655 ኪሎ ኸርዝ በ16 ሜትር ባንድ ወይም በ21555 ኪሎ ኸርዝ በ13 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰተላልፈውን የሬዲዮ ፕሮግራም መስከረም 1 ቀን 2001 ዓ.ም ሐሙስ ምሽት ይጀምራል።

የህዝብ ግንኙነት ክፍል

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዮ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

## ዘመን ተለወጠ - እኛስ? ጋቹዬ

ዛሬ፤ ለኢትዮጵያውያን የአዲስ ዓመት መግቢያ እለት ነው።ታዲያ ይህ አዲስ ዓመት ትርጉም የሚኖረው በአዲስ አስተሳሰብና በአዲስ መንፈስ ስንቀበለው ነው። ያም አዲስ መንፈስ የነፃነት መንፈስ ነው- የፍርሀትንና የባርነትን ትብታብ በጣጥሶ የሚጥል የነፃነት መንፈስ። ዓመቱን በእንደዚህ ዓይነት መንፈስ ካልተቀበልነው፤ሽግግሩ የእድሜ እንጂ የአዕምሮና የልብ አይደሆንም።ያለአስተሳሰብ ለውጥ እንዲሁ፦"ኢዮሀ አበባ፣ ና መስከረም ጥባ" ማለት ደግሞ ፤ አዲስን የወይን ጠጅ በአሮጌ አቁማዳ እንደማስቀመጥ ነው።

**"እኛኮ ለዘመን ክንፎቹ አይደለንም፣**
**ሰንኮፍ ነን ለገላው፣**
**በታደሰ ቁጥር የምንቀር ከሁዋላው"** ያለው ማን ነበር?አዎ!ከዚህ ምድር ሁላችንም ተራችንን እየጠበቅን እናልፋለን።የመኖር ትርጉሙም በእዚህ በሚያልፈው እድሜ ለራስና ለተተኪው ትውልድ የማያልፍ ቁም ነገር ሰርቶ ማለፍ ነው።አበው፦"እወቅ ያለው በአርባ ቀኑ ያውቃል፤ አትወቅ ያለው በአርባ ዓመቱም አያውቅ "እንዲሉ ፤ ይህን ታላቅ ቁም ነገር ለመስራት ደግሞ በእድሜ ማደግና ልጅ መሆን ልዩነት የለውም። ዋናው ነገር በአዕምሮ አድጎ መገኘት ነው።ትናንት ለዛሬ ቦታውን አስረክቦ ሲሄድ፤ ከትናንት ዛሬ አካልና ዕድሜያችን ሲጨምር፤ንቃተ ህሊናችንና የአኗኗር ዘይቤያችን ካልተለወጠና በእዕምሮ ካልጎለመስን፤መቶ ዓመትም ብንኖር ልጆችና ሌሎችን አኗኗሪዎች እንደሆንን ነው የምናልፈው።

ለምሳሌ ፤በቅዱሱ መፅሀፍ ውስጥ በእድሜ ርዝማኔው የሚታወቀው ሰው ማቱሳላ ይባላል። ሆኖም 969 ዓመት የኖረው ማቱሳላ፤ የሚጠቀስበት ጉዳይ ቢኖር፤ ረዥም ዕድሜ በመኖሩ ብቻ ነው- አበው "የማቱሳላን ዕድሜ ይስጥህ" እንዲሉ። በእዚያው መፅሀፍ ውስጥ በለጋነት ዕድሜ ማለፉ የተነገረለት ወጣት ደግሞ አቤል ይባላል። ወጣትነቱ ያለፈው አቤል ግን እነሆ የከወነው ቁም ነገር ዘመናትን ተሻግሮ ይመሰከርለታል፤ ይዘከርለታል።" የአቤልን መስዋዕት የተቀበልክ አምላክ ፤የኛንም ፀሎት ተቀበልልን"እንዲሉ።

በእርግጥም ያለ ቁምነገር ዘመን መቁጠር፣ የልጅ ልጅ መሳም ወይም ሰባት ትውልድ መኖር ፤ ትርፉ ምንድነው?

"መልህቅ አርባ ዓመት ውሀ ውስጥ በኖረ
ተዘፈዘፈ እንጂ መች ዋና ተማረ"

መባሉምኮ ለእዚህ ነው- ያለ አዲስ ለውጥና የዕድገት አስተሳሰብ ዘመንንና ዕድሜን ብቻ መቁጠር፤ ትርጉም የሌለው መሆኑን ለማጠየቅ። ከዚህ አንፃር እኛ ኢትዮጵያውያን ቦታችን የት ነበር? አሁንስ የት ላይ እንገኛለን?እኛ ስለ አክሱም ስልጣኔ ስናውራ፤ አሜሪካ የምትባል አገር ከነመፈጠሯም አትታወቅ ነበር ቢባል ማን ያምናል? ራስ የነበረች አገር እንደ ካሮት አድራ ቁልቁል እየሄደች የውድቀት ጫፍ ላይ ስትደርስስ ምንደነው ማድረግ ያለብን?ከባርነት ወደ ከፋ ባርነት በተሸጋገርንበት ጊዜ የምንቀበለው አዲስ ዓመትም ሆነ ሚሊኒየም ፤እንደ ከሰረ በዓል፤ ቀጭትን ከመጫር አልፎ ምን ትርጉም ይሰጠናል?በተለይም አባቶቻችን፤ከውጭ ወራሪዎች ጋር ተዋድቀው ያስረከቡን ጥንታዊቷና ቀደምቷ አገራችን ፤ነባራዊ መልኳ በፍጥነት እየተለወጠና አድራ እየጫጨች አገርነቷ ጨርሶ ሊጠፋ በደረሰበት በአሁኑ ወቅት ምን እያሰብን ነው? የዘመኑ ገዥዎች እንደ አገርና እንደ ህዝብ የነበረንን ተስፋ አንጠፍጥፈው ሊወስዱብን ሲነሱ፤እኛ ምን እናድርግ?.......

ምነው በአውድ ዐመቱ የተለመደውን ሰላምታ ገድፈህ ቁስላችንን ነካካኸው ትሉኝ ይሆን?ደስታችንን እና ዓመት በዓላችንን ነጥቀውን፤ ምን የቀረን አዲስ ዓመት ኖሮ፤ " እንኳን አደረሳችሁ!" ልበላችሁ ወገኖቼ?ለየትኛውስ ኑሮአችሁ ዘመዶቼ? ጊዜው፤ እንደ ወትሮው እየከፋን፦"ተመስገን" የሚያሰኝ አልሆነም።እንደምናየው የገዥዎቹ ግፍ ሰማይ ደርሷል፤ በደላቸው ፅዋውን ሞልቶ ፈስሷል።ታዲያ በእደዚህ ዓይነቱ ጊዜ ፦ " እንኳን ለ አዲሱ ዓመት አደረሳችሁ" ብላችሁ ፤እናንተንስ አይጎረብጣችሁም?ዓመትባሉና አዘቦቱስ ከተደባለቀብን ሰነበትን አይደል?ለዚህ ነው በዐውደ ዓመቱ " ዕንቁጣጣሽ" በማለት ፋንታ "ምን እናድርግ? " የምላችሁ።በእርግጥም፣በእርግጥም......

ነፃነትን ከማረጋገጥ አኳያ በአዲሱ ዓመት ምን ቁም ነገር እናድርግ?ምን ታሪክ እንስራ? ምን ተግባር እንከውን?መቼም ወቅቱ ታላቅ ተግባርን የሚጠይቅ ጊዜ ለመሆኑ፤ አገርና ወገን ወዳድ ኢትዮጵያውያንን በሙሉ ያለ አንዳች ልዩነት ያስማማናል ብዬ አምናለሁ።ታዲያ ምን እናድርግ? ዝምታውስ እስከመቼ ነው?አገርንና ወገንን የመታደግ ተግባር ከመቼው ጊዜ በላይ ግድ በሆነበት በዚህ ወቅት ፤የገዥዎቹ አፈ-ቀላጤዎች ሆን ብለው የሚረጩት የፍርሀት መርዝ ከነደፈን ወይም የግዴለሽነት አዚም ከተጫነን፤የተለወጠው አዲስ ዘመን የሚደርብልን ነገር ቢኖር ፤እርጅናንና ባርነትን ብቻ ይሆናል። በእርግጥ፤ሁላችንም ባይባል ብዙዎቻችን ዘመን በተለወጠ ቁጥር እኛም አዲስ እንድንሆን፤ እርጅናችን እንደንስር እንዲታደስ፤ ደስታችንና አገራዊ ክብራችን እንዲመለስ እና ነፃነታችን እንዲረጋገጥ የምንፈልግ ህዝቦች ነን። አገራዊ ክብርንና ነፃነትን ለማረጋገጥ ደግሞ፤ከአበው የጀግንነት ውዳሴ ባሻገር መከወን ያለበት ተግባር አለ።" አብርሀም አባት አለኝ' ማለት እንደማያፀድቅ ወትሮም ኢየሱስ ነግሮናል። ስለዚህ እንደ አብርሀም ሆኖ መገኘት ግድ የሚለን ወቅት ላይ ደርሰናል።ርስታችንን(አገራችንን) ፤ በትክክለኛ መልኳ ለይስህቆቻችን (ለልጆቻችን) ማስረከብ የምንችለውና በሚያልፈው ዘመናችን የማያልፍ ቁም ነገር ሰርተን የምናልፈው፤ራሳችን እንደ አበው ስንሆን ነው እንጂ በአበው ታሪክ ስንመካ አይደለም።

ስለዚህ፤ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ፣አዲሱን ዓመት ያለፈቃድህ የተጫነህን የግፍ አገዛዝና የባርነት ቀንበር ፤ከግንቦት 7 ጎን በመቆም ሰብረህ ነፃነትህን ለማረጋገጥ እና በልጆችህ የሚዘከር የማያልፍ ታሪክ ለመስራት ፤ለራስህ ቃል በመግባት በአዲስ የነፃነት መንፈስ እንድትቀበለው ጥሪያችንን እናቀርብልሀለን።

## አጠቃላይ እንቅስቃሴ ቆሟል

ከገጽ 2 የዞረ

እንደ ኤጄንሲው መረጃ፤ ባለሀብቶቹ 25 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ሲሆን፤ ፈቃድ የወሰዱትም በማምረቻ፣ በህንፃ ግንባታ፣ በትምህርት፣በጤና፣ በሆቴል፣በሪል ስቴት፣ በማሽነሪ ኪራይ እና በሌሎች ኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ነበር። ባለሀብቶቹ ወደ ስራ ያልገቡት፤ አ ጠቃላይ የንግድና የ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መቆሙን ተከትሎ አቅማቸው ክፉኛ በመዳከሙ፣ በአስደንጋጭ ሁኔታ ከተተኮሰው የዋጋ ግሽበት ጋር ተያይዞ በባንክ ውስጥ የውጭ ምንዛሬ ጨርሶ በመጥፋቱ እና በኢኮኖሚው ዘርፍ ተስፋ የሚሰጥና ዋስትና የሚሆን ነገር በመታጣቱ ነው ተብሏል።መዋሸት የማይታክታቸው ወይም ብዙዎች እንደሚጠሯቸው'' አቡሀ ለሐሰት'' የሆኑት ገዥዎቻችን፤"ኢኮኖሚያችን በሁለት ዲጂት መመንደጉን ቀጥሏል "ባሉበት ማግስት ትምክህታቸው የሆነው የዓለም ባንክ ባወጣው መግለጫ፤ በኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት 155 በመቶ መድረሱን ና የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ከውጪ ዕቃ ገዝቶ የማስገባት አቅማቸው ክፉኛ መዳከሙን በመጥቀስ፤ ዓለማቀፉ ህብረተሰብ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተስፋ የቆረጠበት ደረጃ ላይ ደርሷል ማለቱ አይዘነጋም።

# የአዲስ ዓመት መልእክት
# ከግንቦት 7 አመራር፣ ከዶ/ር ብርሃኑ ነጋ

ውድ ወገኖቼ!
በመጀመሪያ እንክዋን ለአዲሱ አመት አደረሳችሁ በማለት በራሴና በመላው የግንቦት 7 አባላት ስም፤ ከግንቦት 7 ውጭም በአገራችን ነፃነትና ዴሞክራሲያዊ ስርአት እንዲሰፍን በያሉበት በየራሳቸው የትግል ስልት እየታገሉ ባሉ የኢትዮጵያ ልጆች ስም የመልካም ምኞት መግለጫችን ይድረሳችሁ፡፡
ይህን የአዲሱን የአገራችንን 2ሺ አንደኛ አመት ስንቀበል በኢኮኖሚ ችግርና በመብት ማጣት ምክንያት ከአገራቸው የተሰደዱ ወገኖቻችን ተመልሰው፤ በግፍ የተቀማ መብታቸውን ለማስመለስም ሆነ አገሪቱን በእውነትም የጋራችን ለማድረግ ከዚህ ትእቢተኛ መንግስት ጋር በየጫካው የሚዋደቁት ወገኖቻችን መሳሪያቸውን አስቀምጠው ችግራቸውን በጠረጴዛ ዙሪያ እንደ አንድ የአገር ልጆች ለመፍታት ችለው፤ አገራቸውን ከወራሪዎች ለመከላከል ብለው የገቡት ቃልኪዳን ተረግጦ የትእቢተኞችን ጊዜያዊ የስልጣን ጥም ለማርካት ብለው በአገር ውስጥ ከወገኖቻቸው ጋር፤ በሶማልያ ደግሞ ከጎረቤት አገር ህዝብ ጋር እንዲዋጉና በአሰቃቂ ሁኔታ አስከሬናቸው በየጎዳናው እንዲጎተት የሆኑት ወታደር ልጆቻችን፤ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ወደ አገራቸው ተመልሰውና ለሕዝባቸው ቃል የገቡትን ስራ ብቻ የሚሰሩበት፤ በጊዜያዊ የስልጣን ስሌት ምክንያት በሚደረግ የሚስጥር ሽረባ ምክንያት ከተወለዱበትና ካደጉበት ቀያቸው ተፈናቅለው መኖሪያቸው ለባእዳን ተሰጥቶባቸው መሬት አልባ፣ አገር አልባ፣ እንዲሆኑ የተፈረደባቸው ወገኖቻችን ወደ መንደራቸው የተመለሱበት፤ በተለያየ የስራ መስክ የተሰማሩ የአገራችን ዜጎች ያለምንም ፍርሀትና መሸማቀቅ የማሰብ ችሎታቸውንና ጉልበታቸውን ተጠቅመው ኑሮአቸውን ለማሸነፍ የሚታገሉበት በዚያውም የሚወዱዋትን አገራቸውን ከወደቀችበት አንስተው ወደ ክብር ቦታዋ የሚመልሱበት፣ ብዙሀን ህዝቡዋንም ከአስከፊና አዋራጅ ድህነት የሚያላቅቁበት፤ ሁላችንም ያሉንን ልዩነቶች በሰለጠነ መንገድና በውይይት ፈትተን፣ በውይይት መፍታት ያልቻልነውን ለህዝብ ውሳኔ አቅርበን፣ የሕዝብን ውሳኔ ተቀብለን በሰላምና በተስፋ የምንኖርባት አንዲት አገር ይዘን ቢሆን የምንቀበለው ምንኛ ደስተኞች በሆንን ነበር፡፡ እኛ የግንቦት 7 አባላት በአገራችን ነፃነት ተንሰራፍቶ፤ ሕዝባችን ገዢዎቹ ከከተቱት የፍርሀት ሰንኮፍ ተላቆ፤ በመረጣቸውና ባልተስማማው ጊዜ በድምፁ በሚያነሳቸው መሪዎች፤ እነሱ የሚፈሩት ሳይሆን መንግስት ሕዝቡን የሚፈራበትና የሚያከብርበት፣ የኛ ነው የምንለው አገር ከማየት ውጪ በእዚህ ምድር ላይ የምንምኘው ምንም ነገር የለም፡፡
ይህ ግን ሊሆን አልቻለም!

ይህ ያልሆነው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ይህንን ስላልፈለገ አይደለም፡፡ አንዳንዶች ሊነግሩን እንደሚፈልጉት የኢትዮጵያ ሕዝብ በነፃነት ከመኖር በላይ የሚፈልገው ነገር ስላለ፤ ወይንም፤ ከንቱ ገዢዎቻችን በማያባራ ውሸታቸው ሊያሳምኑን እንደሚፈልጉት ኢትዮጵያውያን ከአገራዊ አንድነታቸው ይልቅ ዘራቸውን፤ በዜግነታቸው ከሚያገኙት ነፃነታቸውና መሪዎቻቸውን መምረጥ ከሚያስችላቸው ዴሞክራሲያዊ ስርአት ይልቅ ከዘራቸው በተወለደ አምባገነን መገዛትን የሚመርጡ ጭፍን ዘረኞች ስለሆኑ አይደለም፡፡ በነፃነት ሰርተውና ጥረው ኑሮአቸውን ከማሻሻል ይልቅ በባርነትና በፍርሀት ሰንሰለት ታስረው መንግስት (እራሱ ከሌሎች) ለምኖ የሚሰጣቸውን የችሮታ ስንዴ ወይም የእድገት ተስፋ መመገብን መርጠው አይደለም፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብማ ምን እንደሚፈልግ፤ ለነፃነቱ ያለውን ቀናኢነት፤ ለዴሞክራሲ ያለውን ፍቅር፤ ዘር ሳይቆጥር የሁሉም መብት እንደዜጋ የሚከበርበት የእኩሎች አገር እንደሚፈልግ፤ በተራ ተዕቢት ጆሮውን የዘጋም ሆነ አይኑን በጊዜያዊ የቁሳቁስ ጥቅም ለጋረደ ሁሉ፤ ምንም በማያወላዳና ለጥርጣሬ ምንም በር በማይከፍት መልኩ በግንቦት 7፣ 1997 እለት ለትእቢተኞቹም፤ለአጫፋሪዎቻቸውም፤ ለመላው የአለም ሕዝብም አሳይቶአል፡፡

ከአሁን የጠማውን ነፃነቱን፤ የአገሩ ባለቤትነቱን፤ እንዴት ያገኘዋል? ይህ የውርደት ኑሮ እንዴት ያበቃል? የሚለው ጥያቄ ብቻ ነው፡፡የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዚህ በላይ ወይንም በዚህ ምትክ የሚፈልገው ነገር አለ ብሎ የሚያምን ማንም ሰው ወይንም ሀይል ይሕንን ጥያቄ በቀጥታ ለሕዝቡ አቅርቦ ሕዝቡ በነፃነት በሚያደርገው ምርጫ ካላሳየን በቀር፤ ከግንቦት 7 ምርጫ በሁዋላ ከዚህ ውጪ በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ለመናገር የሚችል ምንም ምድራዊ ሀይል የለም!
የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!
አሁን በስልጣን ላይ የሚገኙት አይን አውጣ ገዢዎች ምርጫህን እንደ ማጅራት መቺ በጉልበት ከቀሙህ በሁዋላ ይህን ሁሉ ያደረጉት ላንተ ብለው እንደሆነ ያለምንም እፍረት በየቀኑ ይነግሩሀል፡፡ እድገት እያመጣንልህ ነው፡፡ መንገድ እየሰራንልህ ነው፡፡ ስለዚህ ላንተም የሚበጅህ፤ አታውቀውም እንጂ፤ አንተም የምትፈልገው ዝም ብሎ መገዛት ነው፡፡ በታሪክህ ከዚህ ውጭ ምንስ አይተህ ታውቃለህ? ይሉሀል፡፡ ጥቂት ከዚህ ስልጣን ትንሽ ፍርፋሪ የሚወረወርላቸው፤ ወይንም ደግሞ በስልጣን ላይ ከተቀመጡትጉቦኛ ባለስልጣኖች ጋር ተሞዳሙደው አገርና ሕዝብን በመዝረፉ ስራ ላይ የሚተባበሩት ሰዎችም እነሱ ስለተመቻቸው አንተም የተመቸህ መስሎአቸው ‹የኢኮኖሚ ለውጥ እየመጣ ነው፤ እድገት እየተመዘገበ ነው፤ ገበሬው ምርቱንና ገንዘቡን የሚያስቀምጥበት አጥቶአል፤ሚሊየነር እየሆነ ነው፤ ዴሞክራሲም ባይኖር፤ መብቶች ቢጣበቡም አገሪቱ እየተመነደገችና እየሰለጠነች ነው ይሉሀል፡፡ እንዲህ የሚሉህ አንዳንድ ሰዎች ቀለም የቆጠሩ ስለሆኑ ትንሽ ግር ሳያሰኙህ አይቀሩም፡፡ በየቤታችሁ እነኝህ ጉደኞች የሚሉትን ስትሰሙ እናንተ ስለምትኖሩባት አገር፤ እናንተ ስለምትኖሩት ኑሮ ሳይሆን ስለሌላ አለም የሚያወሩ ሳይመስሉዋችሁ አይቀርም፡፡
ገዢዎቻችን ‹የእድገት መንግስት ነን› ለሚል ቅዥታቸውና በዚያውም የአገሪቱን ሕዝብ የዴሞክራሲ ፍላጎት ያዘናጉ መስሎአቸው ሆን ብለው በፈጠሩት የዋጋ ግሽበት አንድ ሽህ ብር በወር የሚያገኝ ሰው ዛሬ ልጆቹን ምን እንደሚያበላ ግራ ገብቶት እግዚኦ በሚልበት አገር፤ ከ90 በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚያ በታች የወር ገቢ በሚያገኝበት አገር፤ በቀን 5 ብር (በወር 150 ብር) የሚያገኝ ሰው ከድህነት ወለል በላይ ነው በሚባልበት አገር፤ የአገሪቱ ሕዝብ አማካይ አመታዊ ገቢ በአመት ከ ሺህ አምስት መቶ የኢትዮጵያ ብር በታች በሆነበት አገር፤ 14 ሚሊዮን የሚገመት ዜጋችን የሚበላው አጥቶ በችጋር በሚጠበስበት አገር ላይ ነው እንግዲህ ሕይወትህ እየተሻሻለ እንደሆነ፤ ዝም ብለህ ከተገዛህ ወደፊትም የበለጠ እንደሚሻሻል ሊሰብኩህ የሚፈልጉት፡፡ ይህን ሲያደርጉ እጅግ የሚገርመው ግን ለሕዝቡ ያላቸው ንቀት ብቻ ሳይሆን የራሳቸውም ድንቁርና ለከት ማጣት ነው፡፡ የዚህ የንቀት ፕሮፓጋንዳ ኣላማው ግን አንተ ኑሮህን አታውቀውም ከሚል አይደለም፡፡ የፕሮፓጋንዳው ጎርፉ፤ በሕይወትህ እየገጠመህ ካለው የድህነትና የችጋር አበሳ ጋር ተደማምሮ ፍፁም ተስፋ እንድትቆርጥና በራስህ ላይ ምንም መተማመን እንዳይኖርህ ቅስምህን ለመስበርም ነው፡፡ ለዚህ ነው ምንም እንኩዋን ፊት ለፊት በሬዲዮንና በቴሌቪዥናቸው ባይናገሩትም ‹ተማርን› በሚሉት ደጋፊዎቻቸውና ፍርፋሪ ለቃሚዎቻቸው በኩል በአገሪቱ ያለው ሁኔታ ያሳስበኛል ብሎ የሚቆጭ ሰው ባገኙ ቁጥር ‹እባክሽ ምን አደከመሽ› ‹የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሆን ፈሪ ነው። ምንም ቢያደርጉት አይነሳም› ይልቅስ አንድ ነገር አደርጋለሁ ብለሽ ራስሽን አትጉጂ፤> የሚል መሰሪ ፕሮፓጋንዳ የሚያካሂዱት፡፡ የግንቦት 97 ምርጫና እንቅስቃሴ ለአንድ ድርጅት ጥቅም ሲባል የተደረገ ይመስል፤ ይህንን ድርጅት ለማፍረስና ለመግደል ሌት →

# የአዲስ ዓመት መልእክት

ከገጽ 4 የዞረ

ተቀን ባላቸው ሀይል ሁሉ ተጠቅመው እንዳልተንቀሳቀሱ ሁሉ ዛሬ ‹ቅንጅት ተከፋፍሎአል፤ ከአሁን በሁዋላ ትግል ዋጋ የለውም፤ አብቅቶለታል፤ ተስፋ ቁረጡ የሚል መርዝም በህዝቡ ዘንድ ይበትናሉ፡፡ ነፃነት ምን እንደሆነ አያውቁምና ሁሉም የሕዝብ ትግል እንደነሱ ጥቂት ሰዎችን ከስልጣን ለማውጣት የሚደረግ ለማስመሰል ቢሞክሩ ግብዝነታቸው ያሳዝነናል እንጂ አይገርመንም፡፡ ይህ ሁሉ ግን አንድ ያነጣጠረበት አላማ አለው፡፡ አላማው ቢቻል ሕዝቡ ሳይከፋው እሺ ብሎ እንዲገዛ፤ ካልሆነም ፍፁም በራሱም ሆነ በወገኑ ተስፋ እንዲቆርጥና ይህንን የወሮበሎች ቡድን በትግል ለመጣል አይቻልም ብሎ እንዲያምን ለማድረግ ነው፡፡ አምባገነኖች እንደተባበረ የሕዝብ ትግል እንቅልፍ የሚነሳቸው ነገር የለም!

በነገራችን ላይ ይህ የወያኔ/ኢሕአዴግ ዘዴ የነሱን ብልህነት የሚያሳይ አዲስ ዘዴ አይደለም፡፡ ጣልያን አገራችንን በወረረ ጊዜ ያደርግ የነበረው፤ ሁሉም አምባገነኖች ሞክረው ያልተሳካላቸው ከንቱ መላ ነው፡፡ ችግሩ አምባገነኖች ሁሉ ከታሪክ አይማሩም፡፡ ጣልያን አገራችንን አስገብሮ ለመግዛት ያለው የጠመንጃ የበላይነት ለብቻው እንደማይበቃ አውቆ ነበር ከማህበረሰባችን የተወሰነውን ‹ትንሽ ያወቀ የሚባለውን› ግብዝ ሆዳም በባንዳነት ገዝቶ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን አርፎ መገዛት እንዳለበት ሲያሰብክ የነበረው፡፡ ጣልያን ብዙ መንገድ እየሰራ ነው፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የተሻለ ሕይወት እያመጣ ነው፤ ዋና ፍላጎቱ አገሪቱን ማሰልጠን ነው፤ የጣልያንን አገዛዝ የሚቃወሙ ጥቅማቸው የተነካባቸው የገዢው ብሄር ባላባቶች ብቻ ናቸው፤ የታላቁንና የገናናውን የጣልያንን መንግስት የሚቃወሙ በቀላሉ ድባቅ ይገባሉ፤ ይልቁንስ ውጤቱ ሕዝቡን ማስጨረስ ብቻ ነው! የሚለውን ፕሮፓጋንዳውን እሱ ብቻ ሳይሆን ለሱ ባደሩ ባንዳዎችም ሲያሰራጭ ነበር፡፡ ዋና አላማውም የሕዝቡን ትጥቅ ማስፈታት፤ የመታገል ወኔውን መስበር፤ የሰውነት ማንነቱንና ክብሩን ማሳጣት ነበር፡፡ ክብር ለአባቶቻችን፤ ለእናቶቻችንና ለአያቶቻችን ይሁንና እንዲህ አይነቱን መሰሪ ፕሮፓጋንዳ ከቁብ ባለማስገባት፤ ለአገራቸውና ለነፃነታቸው ባደረጉት ተጋድሎ ነው ይኸው ከአሰቃቂው የቅኝ አገዛዝ አምልጠን፤ ቢያንስ በኩራት ‹በነፃነቱዋ ታፍራና ተከብራ› የኖረች የምንላትን አገር ያስረከቡን፡፡

እርግጥ ነው አሁን እየረገጡንና እያላገጡብን ያሉት ጣልያኖች አይደሉም፡፡ የገዛ አገራችን ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ ግን ያለንበትን ሁኔታ የበለጠ እንዲያንገበግበን የሚያደርገን እንጂ በአገራችን ሰዎች እጅ የሚደርስብንን የነፃነት ማጣትና ውርደት በፀጋ እንድንቀበለው የሚያደርገን አይደለም፡፡ ጣልያንስ የአውሮፓ ነጮች በዘመናዊ ስልጣኔ ያንሱናል ብለው ይንቅዋቸው የነበረውን ጥቁሮችን ያይበት ከነበረው የተንሸዋረረ የትምክህት መነፅር ተነስቶ ማንነታችንን፤ ባሕላችንን፤ ለነፃነት ያለንን ቀናኢነት ባለመረዳት ያደረገው ነው እንበል፡፡ እነኝህን የኛን ጉዶች ምን ልንላቸው ነው? በስልጣን ላይ ያሉት ሰዎች ስለራሳቸው ምን ቢያስቡ፤ ሌሎቻችንን እንደምን ቢወስዱን፤ ከኛ በምን የተሻልን ነን ብለው ቢያስቡ ነው በጉልበት አስገድደውና አስገብረው፤ በተራ ውሸት አጭበርብረው፤ ሊገዙን የሚፈልጉት? አገራችን ለሚሉት አገርና ሕዝባችን ለሚሉት ሕዝብ ምን አይነት አመለካከት ቢኖራቸው ነው ልክ እንደ ጣልያን መንገድ ስለሰራንልህ አርፈህ ተገዛ የሚሉን? በማን ንብረት ለሰሩት መንገድ ነው እኛ ተገዢያቸው እንድንሆንላቸው የሚመኙት? እንዴት ነው ከዚሁ ከምስኪን ድሀ ሕዝብ እየዘረፉ እራሳቸውን አበልፅገው፣ መልሰው በዚሁ ገንዘብ ባበጠ ልባቸው ሌላውን ለመናቅና ለማዋረድ የሚከጅሉት? እነሱ ከማን ተፈጥረው ጀግና ሆነው ነው ሌላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈሪ የሚሉት?

እንደምንተዋወቅ እረሱት እንዴ!

ውድ ወገኖቼ!

ማርም ሲበዛ እንደሬት ይመራል ይላል ያገራችን ሕዝብ፡፡ የተለያዩ አገዛዞች በተለያየ ስም ሲረግጡን ከረሙ፡፡ ከሁዋላችን በአብዛኛው በመረጡዋቸው መንግስቶች በነፃነት በሚኖሩበት አለም፤ እኛ የቀደምት ስልጣኔ ወራሾች ነን የምንለው ጥላችንን በምንፈራበት የፍርሀት አገዛዝ ተጠፍረን፤ በረሀብ አለንጋ እየተገረፍን ልንኖር በፍፁም አይገባንም፡፡ ገዢዎቻችንን በቃችሁ እንበላቸው፡፡ የአሁኖቹን ባለጊዜዎች ብቻ ሳይሆን ከዚያም በሁዋላ በማንምና በምንም ስም ነፃነታችንን ገፎ፤ እኛ እንደ ሕዝብ ሳንመርጠውና ሳንፈቅድለት ማንም ሊገዛን እንደማይገባና እንደማይችል ለአንዴም ለሁሌም እናሳይ! በምርጫ 97 ጊዜ በግልፅ ያሳየነውን የነፃነት ፍላጎታችንን በጋራ ትግላችን የምንጎናፀፈው ቢሆንም፤ ያለነፃነትና ፍትሕ አልኖርም የሚለውን እምቢተኛነት መወሰን ያለብን ግን እያንደንዳችን በግላችን ነው፡፡ በ 1997 ምርጫ ወቅት በተደጋጋሚ ለመግለፅ እንደሞከርኩት ትግላችን ሌላውን ነፃ ለማውጣት ሳይሆን እራሳችንን ነፃ ለማውጣት ነው፡፡ ይህ የአሁኑ ትግላችን የምርጫ 97 ቀጣዩ አካል ነው፡፡ በምርጫው ወቅት እያንዳንዳችን እንደግለሰብ፤ ሁላችንም እንደ ሕዝብና እንደ አገር የምንፈልገውን አሳውቀናል፡፡ ይሕንን ፍላጎታችንን በሀይል የቀማንን ሀይል ግድ የለም ብለን፤ ጉዳዩን ለፈጣሪያችን ሰጥተን የምንተወው አይደለም፡፡ ፈጣሪያችንማ ከኛ የሚፈልገውን ሲፈጥረን ግልፅ አድርጎልናል፡፡ ነፃ ሰዎች አድርጎ ፈጥሮናል፡፡ ነፃ ሆነን የተፈጠርን ሰዎች በደልን፤ ፍትሕ ማጣትንና ባርነትን በዝምታ ከተቀበልን የምናሳዝነውና የምናሳፍረው ልጆቻችንን ብቻ ሳይሆን ፈጣሪያችንንም ነው፡፡

ውድ የኢትዮጵያን

የግንቦት ሰባት የፍትሕ፤ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የምርጫ 97 ቃልኪዳን ውልድ ነው፡፡ ይህ የነፃነትና የዴሞክራሲ ቃል ኪዳን እውን እስከሚሆን ድረስ ባለን አቅማችን፤ ለፍትህና ለዴሞክራሲ እንዲሁም ለኢትዮጵያ አንድነት ከሚታገሉ ሀይሎች ጋር ሁሉ ተባብረን በኢትዮጵያችን ለአንዴና ለሁሌም የአገዛዝ ስርአት የሚወገድበትን መንገድ መፈለግ፤ ለዚያም አስፈላጊ ነው ብለን ባመንነውና ሕዝቡን በቀጥታ በማይጎዳ፤ ይልቁንም ሕዝቡን በሰፊው ባስተባበረ ሕዝባዊ ትግል እስከመጨረሻው ለመታገል የቆረጥን ወገኖችህ መሆናችንን የግንቦቱን ቃላችንን በማደስ በድጋሚ ቃል እንገባልሀለን፡፡

ይህ የነፃነት ፍላጎታችን በሰላማዊ መንገድ፤ እነኝህን በትእቢት የተወጠሩና በሕዝባችን ላይ ብዙ በደል የፈፀሙ ሰዎችንም አካቶ፤ ከተንኮልና ከሸር በፀዳ፤ በእውነተኛና ግልፅ መንገድ፤ የአገሪቱ ጉዳይ የሚመለከታቸውን ሀይሎች በሙሉ በእርቅ መንፈስ አስቀምጦ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ በሚሳተፍበት መልክ ቢፈታና፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ በመረጠው መሪዎቹ የሚተዳደርበት፤ የተቀረነው ደግሞ ሁላችንም ለአገራችን ባለችን አቅም እንደየሙያችን አስተዋፅኦ አድርገን ልንኖርበት የምንችልበትን አገር ለመፍጠር ብንችል ከኛ በላይ የሚደሰት የለም፡፡ ለእንዲህ አይነቱ የሰለጠነ የመፍትሄ መንገድ ምንጊዜም ክፍት ነን፡፡ አንድ ነገር ግን ፍፁም ግልፅ እናድርግ፡፡ በግንቦት ሰባት ስር የተሰባሰብን ወገኖቻችሁ በምንም አይነት ሰላምን ከነፃነት አንመርጥም፡፡ ለሰላም ያለን ጥልቅ ፍቅር ነው ባርነትን በምንም አይነት እንዳንቀበል የሚያደርገን፡፡ ይልቁንም ነፃነት በሌለበት ሰላም ይኖራል ብለን በፍፁም አናምንም፡፡ ይህም እምነታችን የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እምነት ነው ብለን በፅኑ እናምናለን፡፡

በሀገራችን የሰላምን መንገድ የረገጠውና አገራችንን እያደር ወደ መቀመቅ እየከተተ ያለው ሀይል አንድ ብቻ ነው፡፡ በመለስ፤ በበረከትና በስብሀት የሚመራው የጥቂት ገዢዎች ቡድን፡፡ በኛ እምነት፣ አይደለም ሌላው ሕዝብና አብዛኛው፣

ወደሚቀጥለው ገጽ ዞሯል→

# የአዲስ ዓመት መልእክት
ከገጽ 5 የዞረ

ወታደር፤ ከመጀመሪያ ጀምረው ከደርግ ወራዳ አገዛዝ ለመላቀቅ የታገሉት የሕወሀትና የብአዴን ታጋዮችም እነኝህን የሙት ጉዋዶቻቸውን አደራ የበሉ ጥቂት ትእቢተኞች በስልጣን ለማቆየት ብለው፤ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ለዚህ አበሳ ይዳርጋሉ ብለን አናምንም፡፡ ስለዚህም ይህ ትግል እነሱንም የሚጨምር የመላ አገራችን ሕዝብ ትግል ነው ብለን ከልባችን እናምናለን፡፡
ኢትዮጵያ አገራችንን በጣም እንወዳታለን፡፡ ያለችን ይህችው አንድ አገር ብቻ ነች፡፡ በተለያዩ የአገዛዝ ስርአቶች የተነሳ በታሪክ ብዙ በደል የደረሰባቸው ዜጎቻችን እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ ብዙዎቻችን በአንድ መልኩ ወይንም በሌላ ተበድለናል፡፡ እንደግለሰብ ሁላችንም ተረግጠናል፡፡ ገሚሶቻችን እንደ ባሕል ስብስብ ብዙ በደል ደርሶብናል፡፡ ይሕንን የታሪክ ቁሻሻ በአንድ ጊዜ ጠርገን ማጥፋት ብንችል ምን ያህል ደስተኞች በሆንን ነበር፡፡ ጊዜ ይወስድብን ይሆናል፡፡ ብዙ የስነልቦና ትግል ከራሳችን ጋር ማድረግ ይኖርብናል፡፡ በእርግጠኝነት መናገር የምንችለው ግን ትግላችን ስላለፈው ሳይሆን ስለወደፊቱ መሆን አለበት፡፡ ያሉብንን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ተከፋፍለን መፍታት አንችልም፡፡ ተባብረን፤ እጅ ለእጅ ተያይዘን፤ ከመሀላችን የደከመውን እያነሳን ነው እንደ አገርና እንደ ሕዝብ ወደፊት መሄድ የምንችለው፡፡ እንደ አገርና እንደ ሕዝብ የሚያስተባብረን ደግሞ ፍትሕ፤ የዜግነት እኩልነት፤ ነፃነትና የመብቶች መከበር ነው፡፡ ለዚህ ነው ከዚህ በፊት ከደረሰባቸው በደል በመነሳትና በኢትዮጵያ ማእቀፍ ውስጥ ሆኖ መፍትሄ ማግኘት አይቻልም ብለው ያስቡ የነበሩ ሀይሎች ለሁላችንም እኩል የሆነች፤ በነፃነትና በመተሳሰብ ላይ የተመሰረተች የጋራ ኢትዮጵያን በጋራ መገንባት እንችላለን፤ በመከፋፈል ለበዳዮቻችን፤ ለዘላለም ረግጠው ሊገዙን ለሚፈልጉ መሳሪያ መሆን የለብንም የምንለው፡፡ ለእነኝህ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንም ነው ይህንን የጋራ የትግል ጥሪ በዚህ አዲስ አመት የምናቀርብላቸው፡፡
ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፡፡
ዛሬ ያለፈውን ምሬታችንን እያነሳን የምንብከነከንበት ቀን አይደለም፡፡ ዛሬ ማሸነፉ ምንም የማይቀረውን አዲስ የትግል ምዕራፍ በጋራ የጀመርንበት ቀን ነው፡፡ ያለፈውን የሰቆቃ አመት እያስታወስን የምንቆዝምበት ሳይሆን በጋራ ትግላችን አዲስ የድል ምእራፍ የምንከፍትበት የተስፋ ቀናችን ነው፡፡
ግንቦት 7 ይህንን ሬድዮ በመክፈት ከመላው ሕዝባችን ጋር የምንገናኝበትን መስመር ዘርግትዋል፡፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በግሉ ለነፃነቱ የተቻለውን ለማድረግ ቃል የሚገባበት ቀን ነው፡፡ ሁሉም እራሱን ለጥቃት ሳያጋልጥ እኔ ምን ብሰራ ትግሉን እጠቅማለሁ ብሎ እራሱን የሚጠይቅበትና በግሉም ሆነ ከሚያምናቸው ጥቂት ጉዋደኞቹ ጋር በመሆን ለትግሉ አስተዋፅኦ የሚያደርግበት ነው፡፡ የግንቦት 7 ሬድዮም ይህንን ትግል በማስተባበር፤ የምናደርጋቸውን የጋራ እንቅስቃሴዎች በማገናኘት የበኩሉዋን ትወጣለች፡፡በያለበት የሚገኙ የግንቦት 7 አባላትና ደጋፊዎችም ትግሉን የሚያካሂዱበትን ስልት የሚያቀናጁበት፤ ከሌሎች የፍትህና የነፃነት ታጋዮች ጋር ትግሉን በያካባቢያቸው የሚያስተባብሩበትን መንገድም አመቻችተን በቅርቡ ለሕዝብ እናስታውቃለን፡፡ በጋራ የምንወስዳቸውን ሕዝባዊ የእምቢተኝነት እርምጃዎች እንደየሁኔታው ከሕዝቡ ጋር የምናስተባብርበት መድረካችንም ፤ግንቦት 7 ሬድዮ፡፡ አድምጡዋት፤ ተከታተሉዋት፤ መልእክቱዋን ከምር ውሰዱት፤ ተቀላቀሉን!
የጋራ ትግላችን አጋር ሁኑ!
በዚህ አጋጣሚ ስለፍቅር፤ ስለሰላም፤ ስለእርቅ ማንጎራጎር ሀጢአት ሆኖ በእስር እየተሰቃየሕ ያለኸው ወገናችን ቴዲ አፍሮና ሌሎችም በግፍ፤ ፍፁም በሚያሳፍርና በተበላሸ የፍትሕ ስርአት ስር በየማጎሪያው እየተሰቃያችሁ ያላችሁ ወገኖቻችን በሙሉ ሁሌም ከሀሳባችን እንደማትለዩ፤ ‹የፍትሕ ያለህ› ጩኅታችሁን እየሰማነው እንደሆነ ልንገልፅላችሁ እንወዳለን፡፡

መልካም አዲስ አመት
ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!

## ቃል ኪዳን እንግባ

አዲስ አመት ነውና። አይቀር መመኘታችን። ማለማችን፡፡ ፈጣሪያችንን መማለዳችን። መጪውን አመት የጤና የሰላም የብልጽግና አድርግልን ማለታችን። አዎን! የመልካም ተግባርና ውጤት መነሻው ቀና ምኞትና ህልም፣ ተማጽኖና ምልጃ እንደሆነ እናውቃለን፡፡ ምኞት፣ ህልም፣ ምልጃ ግን ብቻውን አይበቃም፡፡ በመመኘትና በማለም ከረሃብ እራሱን ያዳነ፣ ጤናውና መብቱ ያስጠበቀ ህዝብ በሰው ልጆች ታሪክ ተከስቶ አያውቅም፡፡ ፈጣሪ ከፍጥርት ሁሉ የተለየ አድርጎ በአምሳሉ የፈጠረው ሰው፣ በፈጣሪ የታደለውን አቅም፤ አእምሮና ህሊና ከሰውነቱ አውጥቶ ጥሎ ፈጣሪን ቢማለድ ፈጣሪን ያስቆጣል እንጂ ከሰማይ ዳቦ አያዘንምም፡፡ ሰይፍ ያያዘ መልአክ ከአፈና ነጻ ሊያወጣው፣ መብቱን ሊየስከብርለት በእሳት ታጅቦ ወደ ምድር ሲወርድ ማየት አይችልም፡፡ እንዲያውም ፈጣሪ በአምሳሉ ፈጥሮ ያከናነበውን ነጻነት፣ በሰውነቱ ሊገሰሱበት የማይገቡ መብቶቹን ለማስከበር የማይጥር ሰው ከፈጣሪ የሚጣላ እንጂ ከፈጣሪ ሃዘኔታን የሚያገኝ አይሆንም፡፡ ስለእዚህ ነው መጪው አመት የተሻለ እንዲሆን ምኞት፣ ህልም፣ ተስፋና ምልጃ ብቻቸውን አይበቁም የምንለው፡፡ ኢትዮጵያን ለሁሉም ልጆቿ ሲኦል እንድትሆን ያደረጋት ምንድነው? ለምንድነው የረሃብ፣ የበሽታ፣ የጣርና የመከራው ዶፍ አላባራ ያለው? ለምንድነው ላለፉት ዘመናት የአባት የእናቶቻችንን የወንድም የእህቶቻችንን ክቡር ሕይወት በገፍ መባ ከፍለን የጪሰኛነትና የገባርነት ዘመንን እንዲያከትም ማድረግ ያልቻልነው? ለምንድነው በአፈናና በረገጣ ጉምና ጽልመት የተሸፈነው ጨለማ የማይገፈፈው? የልቅሶ የዋይታ፣ የመግልና የደም አዙሪት አላበቃ ያለው? እረ መቼ ነው የሚነጋው ሌሊቱ? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡
ከልባችን፣ ከምራችን ከጠየቅን ፍዳና ጣእር አምራቾቹ ዛሬ በምኒልክ ቤተ-መንግስት ወዶ ገባ እስረኛ ሆነው በጠምነጃ ተከበው እንደኖሩ በጠመንጃ ለማለፍ የወሰኑት፣ የነጻነት ትርጉም የማይገባቸው ገዥዎቻችንን ብቻ እንዳልሆኑ እንረዳለን፡፡ የኛም ጥፋት፣ የኛም ደካማነት እንዳለበት ያኔ ማየት እንችላለን፡፡ በቃችሁ አለማለታችን፡፡ አሁንስ በዛ አለማለታችን፤ መብትና ነጻነት፣ በሃገር ተከብሮና ታፍሮ መኖር የገዥዎቻችን ችሮታ ሳይሆን የዜግነት ጌጥና ሽልማታችን ነው ብለን በእልህ አለመነሳታችን መሆኑን መረዳት አንችላላል፡፡

ቃል የምንገባው
ነጻነታችንን የገፈፉትን ቸል ላንል
መብታችንን የሚረግጡትን በዝምታ ላናልፍ
ሀብታችንን የሚዘርፉትን እጃቸንን አጣጥፍን ላናይ
ሀገራችንን የሚክዱትን በትዝብት ላንመለከት
ለሰዎች ተንበርካኪዎች በመሆን ፈጣሪያችንን ላለማሰቀየም መሆን ይገባዋል፡፡
ይህንን ለማድረግ ከወሰንና በስራ ለማዋል ቆርጠን ከተነሳን መጪው አመት መልካም ይሆናል፡፡
መልካም አዲስ አመት